# ኑዛዜ ዘያሬድ

**ጁላይ አንድ ቀን 2007 አም**
**በርተንስቪል፣ ሜሪላንድ**
**ያሬድ ጥበቡ**

የቅንጅት አለምአቀፍ አመራር ላዕላይ ምክርቤትን ጉባኤ ከተሳተፍኩ ወዲህ ያለፈው የአንድ ሳምንት ጊዜ (ከጁን 23 እስከ ዛሬ ጁላይ አንድ ቀን ድረስ) በጣም እንቅልፍ ያጣሁባቸው፣ የተረበሽኩባቸው ቀናት ነበሩ ። የእንቅልፍ ማጣቴም ምክንያት ከህሊናዬ በመጣላቴ የተነሳ አልነበረም ። ጆሮዬ ላይ ስልክ የጠረቀሙብኝ፣ በኢሜይል የተማጠኑኝ፣ በአይናቸው ቂጥ በሾርኔ ያዩኝ ጥቂት አልነበሩም ። በዚያው መጠንም፣ ገና ሳያናግሩኝ ውሳኔዬን ያከበሩ፣ ተከራክረውኝ ያቀረብኩትን ምክንያት ተረድተው ድጋፋቸውን የሰጡኝም ጥቂት አይደሉም ። ለመሆኑ ይህ እንቅልፍ የነሳኝ ጉድ ምን ይሆን? አንዳንዶች እንደሚያወሩት ከጓደኛዬ አንዳርጋቸው ጋር ስለተቆራረጥኩ፣ ወይንም ከንቲባ ብርሃኑን «ከድቼ» ከአቶ ሃይሉ ሻውል በመወገኤም አይደለም ። ብርሃኑና አንዳርጋቸው፣ ለትግሉ ይጠቅማል ብዬ ያደረግሁት መሆኑን እንደማይጠራጠሩ እምነቱ ስላለኝ፣ በአሠራር ጉዳይ ላይ በተፈጠረ ልዩነት በአመታት የተገነባ ጉዋደኝነታችንን የሚነካ ይሆናል የሚል ግምት የለኝም ። አለበለዚያማ ጓደኝነታችን፣ አንዳችን በሌላችን የፖለቲካ ፍልስፍና እየተመራን፣ አንዳችን ለሌላችን ፍላጎት እንድናድር እያስጎበደድን ስለሚያደርገው፣ የጨዋነትን ዳራ የሚጋፋ ስለሚሆን ሁላችንም ለዚህ አይነቱ ጓደኝነት የምንጓጓ አይደለንም ብዬ አምናለሁ ። ምክንያቱም፣ ጓደኝነታችን ከዚህ የዘለለና የጠለቀ በመሆኑ ። አሥርተ አመታትን በዘለቀው ዝምድናችንም፣ ከድርጅታዊ አሰራር ጉዳዮች በላቁ የፖለቲካ አመለካከት የተለያየንባቸው ወቅቶች ስለነበሩ፣ ዛሬ በየቡናቤቱ ለሚወሻክተው ፖለቲከኛ የሚያረካ መልስ ማግኘት አይቻለንም ። ፈረንሳዮች «ቪቭ ላ ዲፌራንስ»፣ ወይም ልዩነት ለዘላለም ይኑር! የሚሉት ያለምክንያት አይመስለኝም፣ ሃሳብ ለሃሳብ ሲሞሻለቅ ነው እድገት የሚገኝ ማለታቸው ይመስለኛል ።

እንዴት የቅንጅት አለምአቀፍ አመራር ምክርቤት ጉባኤ ውስጥ ልሳተፍ ቻልኩ? ሁሉም እንደሚያውቀው ስሜ በድረ-ገፅ ከተጠቀሱት አስራአንድ ሰዎች መሃል አይደለም ። በጓሮ በር ነው የገባሁት ማለት ይቻላል ። እንዴት ሊሆን ቻለ? የአለምአቀፉ አመራር አባላት መሃል የተነሳውን ችግር ለመፍታት ከሃገር ቤት በድርጅቱ ሊቀመንበር በአቶ ሃይሉ ሻውል የተላኩት ሁለት የቅንጅት ላዕላይ ምክርቤት አባላትና የፓርላማ ተመራጮች ሁለቱን ቡድኖች ለማስማማት ያደረጉት ስድስት ወራት የፈጀ ጥረት እልባት ያገኘው ከጥቂት ሳምንታት በፊት ከቃሊቲ አመራር የተላከው የምሬትና የምልጃ ደብዳቤ ከቀረበ በሁዋላ ነው ። ሆኖም በዚያው ሳምንት የምክርቤቱ መቋቋም ዜና ከተበሰረ በሁዋላ፣ አለም አቀፍ አመራር (አአአ) ውስጥ ሌላ ክፍፍል መፈጠሩንና ስድስት ለሁለት መከፈላቸውን ተማርኩ ። ይህ መከፋፈል ከተጠራው የምክር ቤት መሥራች ጉባኤ ጋር ተዳምሮ ድርጅቱን ወደመሰንጠቅ እንዳይመራ ለማግባባት እንድችል ሽማግሌዎቹ ባቀረቡልኝ ጥያቄ ነበር፣ በጉዳዩ የገባሁበት ። አንግባ ካሉት ስድስት አባላት መሃል፣ አቶ አንዳርጋቸውን ማግባባት ከተቻለ፣ የቀሩትን እርሱ ያሸንፋቸዋል ከሚልም ሰሌት ነበር ልዑካኑ እኔን የቀረቡኝ ። በወቅቱ እኔም ወደምክርቤቱ አንገባም ብለው አሻፈረን ካሉት ወገኖች ጋር የምቀራረብ ስለነበር፣ ከአንዳርጋቸው ጓደኝነት በተጨማሪም ዶ/ር ገብርዬ የግል ሃኪሜም ስለሆነ፣ ከአቶ ዳንኤል አሰፋ ጋርም ወዳጅነት መሥርተን ስለነበር፣ ሽማግሎቹ ትክክለኛ ምርጫ ማድረጋቸው ተሰምቶኝ ነበር ። ሆኖም፣ የኔም አመለካከት ከነአንዳርጋቸው የሚለይበት ምክንያት ስላልነበር፣ ሽማግሌዎቹ ከነ«ሻለቃ ዮሴፍ ቡድን» ነፃ ናቸው ብዬ ለማመን እቸገር ነበር ። በመጀመሪያው ቀን የጁን 16 ግንኙነቴም ከሻለቃ አድማሱ ጋር በአይቤክስ ምግብ ቤት ባደረግነው ውይይት፣ ይህንኑ የሽማግሎቹን ነፃነት የሚያጠያይቅ ጉዳይ ላይ ተወያየን ። በሌላ ቀን ዶ/ር በዛብህ በተገኙበት ልንነጋገርም ተቃጠርን ። ጁን 20 ቀን ከሥራ በሁዋላ 6:30 ላይ ሲልቨር ስፕሪንግ ከሚገኘው የስታርበክስ ቡናቤትም ተገናኘን ። የሽማግሎቹን ነፃነት የሚረጋግጥልኝ

የነርሱ ንግግር ሳይሆን፣ ስድስት ወራት በቆዩባቸው ጊዜያት የተለዋወጡአቸው ዶሴዎች መሆናቸውን በማመን፣ ያንን እንዲያሳዩኝ አጥብቄ ጠየቅሁ ። እነርሱም ለማሳየት ያለማመንታት ፈቃደኛ ሆነው፣ ተያይዘን ከሲልቨር ስፕሪንግ ቨርጂኒያ ወደሚገኘው ማረፊያ አፓርትመንታቸው አመራን ። ሁለቱም በእጃቸው ያሉትን ደብዳቤዎችና ዶሴዎች ከመኝታ ክፍላቸው አምጥተው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጡልኝ ። እስከ እኩለ ሌሊት መቃረቢያ ድረስ ሳጠናና ሳገላብጥ ቆይቼ፣ «ዋሽንግተን ውስጥ ስምና ዝናችሁ በመጉደፉ አዝናለሁ፣ እናንተ ሃቀኛ ሽማግሌዎች ናችሁ፣ ባነበብኩት ሁሉ አንዳችም ወገንተኝነት አላየሁም፣ እንዲያውም ወገንተኝነት ካለ፣ የነአቶ አንዳርጋቸው ቡድን ለሥራ የተሻለ ችሎታ አለው ብላችሁ የምታምኑ መሆኑ ብቻ ነው ። እኔ ነፃነታችሁን አምኛለሁ፣ አንዳርጋቸውንም ተመሳሳይ አመለካከት እንዲይዝ ለማግባባት እሞክራለሁ» ብዬ ተሰናበትኳቸው ። ለሥራ ወደአውስትራሊያ ተሰማርቶ ከሚገኘው አንዳርጋቸው ጋርም በኢሜይልና በስልክም ተወያየን ። ሆኖም አንዳርጋቸው ከሽማግሎቹ ነፃነትም በበለጠ አይጋ ላይ በወጣው የሻለቃ ዮሴፍ ደብዳቤ እጅግ አዝኖ ስለነበር፣ «እነዚህ ሰዎች ቅንነት ይጎድላቸዋል፣ አብሮ መሥራትም አይቻልም፣ መሪዎቹ በድርድር ሊፈቱ ሳምንት ስለቀራቸው፣ ውክልናቸውን አስረክቤ በይደር ወደተውኳቸው የጥናትና ምርምር ሥራዎቼ እመለሳለሁ»፣ በሚለው ሃሳቡ ፀና ። የኔም ተልእኮ ከሸፈ ። አርብ እለትም ይህንኑ ለሽማግሌዎቹ አቀረብኩ ። እነርሱም ምንም እንኳ ጉባኤው ቅንጅትን ከመሠረቱት አባል ድርጅቶች የዘለለ መሆኑን ቢተማመኑም፣ ከነባሩ የቀስተደመና ወገን አንድም ሰው የማይገኝ መሆኑ ከንክኗቸዋል ። በጉባኤው እንድገኝም ጠየቁኝ ። በታዛቢነት ለመገኘት ተስማማሁ ። አርብ ምሽት ይህንኑ ሁኔታ ከዶ/ር ገብርዬና አንዳንድ ማወቅ አለባቸው ብዬ ካመንኩዋቸው ሰዎች ጋር ተወያየሁ ። አርብ ማታ ሽማግሎቹ ተሳትፎዬ በታዛቢነት የታገደ ሳይሆን ለመምጣት ባልፈቀዱት የነፃ ጋዜጠኞች ማህበር ሊቀመንበር በአቶ ክፍሌ ሙላት ምትክ እንዲሆን ጠየቁኝ ። «ለመወሰን ጊዜ ያስፈልገኛል፣ አሁን ደግሞ በቂ ጊዜ የለም፣ ጠዋት ስመጣ እንወያይበታለን» ብዬ በይደር ተውኩት ። በማግስቱም ድጋሚ ሽማግሎቹ ሲጠይቁኝ፣ «የቃሊቲ አመራሮች ይጠየቁና ካመኑበት እሳተፋለሁ» ብዬ ቃሌን ሰጠሁ ። በዚህም አቶ ሃይሉ ሻውል ተጠይቀው መስማማታቸው ተነገረኝና ጉባኤው ሲጀመር፣ ሙሉ ተሳታፊ ሆኜ የተመደበልኝን መቀመጫ ያዝኩ ።

ለምን የቅርብ ጓደኞቼን ትቼ በ«ፖለቲካ ጠላትነት» ሲያዩኝ ከነበሩ ሰዎች ጋር በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ለመቀመጥ ወሰንኩ? ብዙ ምክንያቶች ነበሩኝ፣

1. ጉባኤው ውስጥ ሳይገቡ ከቀሩት የአለም አቀፍ አመራር አባላት ጋር ቅርበት ስላለኝ ሃረግና ድልድይ ሆኜ አገለግላለሁ ብዬ ተስፋ አድርጌአለሁ
2. ወደጉባኤው ከመጡት የ«ሻለቃ ዮሴፍ ቡድን» አባላት ሊሰነዘር የሚችል፣ ጉባኤው ላይ ያልተገኙትን የማባረር ውሳኔ እንዳይኖር መከላከል እችላለሁ ብዬ በራሴ ተማምኛለሁ፣ ይህም ለድርጅቱ አንድነት ይጠቅማል ብዬ አሰላስያለሁ
3. በጉባኤው ካልተገኙት የአለም አቀፍ አመራር አባላት መሃል፣ ባልተገኙበትም ለሚመጥናቸው ሃላፊነት እንዲመረጡ መታገል እችላለሁ ብዬ አምኛለሁ ። በተለይ አንዳርጋቸው የድርጅት ጉዳይ ሃላፊነቱን ይዞ እንዲቀጥል ማድረግ፣ ለድርድር ሊቀርብ አይችልም ብዬ ወስኛለሁ
4. የአለም አቀፉ አመራር ባለፉት ዘጠኝ ወራት ካደራጃቸው ቻፕተሮች፣ በመዋቅራዊ ቦታቸውም ሆነ በግል ችሎታቸው የመሪነት ብቃት ያሳዩትን እነ ሉሲት መስፍንና የሰሜን አሜሪካው ቻፕተሮች መሪን የመሳሰሉ ታታሪዎችና የአውሮፓ ባልደረቦቻቸው ወደዚህ ምክርቤት ገብተው በፖሊሲ ደረጃ ለሚደረጉ ክርክሮች አስተዋፅኦ የሚያደርጉበት መንገድ እንዲኖር፣ ጉባኤው እንዲወስን መታገል እችላለሁ ብዬ አውጠንጥኛለሁ ።
5. እነዚህን ሁሉ ለማድረግ የሚያስችል ምሁራዊ ብቃትና ፖለቲካዊ ስሱነት ያለው፣ ከነ«ሻለቃ ዮሴፍ ቡድን» ጋር ያልወገነ አዲስ ደም ወደ ድርጅቱ ተቀላቅሎአል ብዬ አምኛለሁ ። ስለ 11ዱ ሰዎች ምንነት በነቂስ ለማጥናትና፣ ጀርባቸውን ለማወቅ ባደረግሁት ጥረት፣ በአመዛኙ ከትግሉ ምንም ጥቅምን የማይሹና፣

እውቀት፣ ጊዜና ገንዘባቸውን ለመሰዋት፣ ለታሰሩት ድምፃቸውን ለማዋስ የፈቀዱ ዜጎች መሆናቸውን ተረድቻለሁ ። የ«ሻለቃ ዮሴፍን ቡድን» ለማዳን ወይም በሥልጣን ለማቆየት የመጡ ናቸው የሚለውን የአለም አቀፍ አመራር ጥርጣሬ ፍፁም ቦታ አልሰጠሁትም ። ዶ/ር ታዬንና ዶ/ር አክሎግን የመሠሉ ሰዎችን በዚህ ለመጠርጠር የሚችል ጤናማ አእምሮ ልረዳው የምችል አልነበረም ።

6 - «ትብብር ለነፃነትና ዴሞክራሲ» ጊዜው የመጣለት ሃሳብ ነው ። ገዢውን ፓርቲ ጭምር ያካተተ የሁሉም የፖለቲካ ሃይሎች ጉባኤ፣ አቶ መለስ እሬት እሬት፣ ኮሶ ኮሶ እያላቸው እንዲውጡ የሚገደዱት እንክብል ነው የሚል አመለካከት ከያዝኩ ሰንብቻለሁ። የዚህ ጅማሮ የጀርባ አጥንት ሊሆን የሚችለው «የኦሮሞ ነፃነት ግንባር» አጋር አጥቶ በር እያንኳኳ ከደጅ ቆሟል ። ቅንጅቱ የገባበት መዳከምና እርስ በርስ መናቆር አክትሞ፣ ወደሥራ ፊቱን እንዲመልስና፣ የተቋረጠውን የትብብር ሥራ ከዳር ለማድረስ፣ ከጉባኤው ውጪ ከቀሩት አካላት ይልቅ፣ ጉባኤው ውስጥ የተገኙ ትና ዩትሬክት ሆላንድ ላይ የትብብሩን ሰነድ የፈረሙት ወገኖች ድጋፍ ይገባቸዋል ብዬ አምኛለሁ ። ጉባኤውም በትብብር ጉዳይ ላይ ቀና ውሳኔዎች እንዲያሳልፍ ጉልህ ሚና መጫወት እችላለሁ ብዬ አሰላስያለሁ ። ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያትም ከሀብረት ጋር ለሚደረግ የትግል አንድነት አዳብሮ የቆየው ግንኙነት ይጠቅማል ብዬ አምኛለሁ ። ከሞላ ጎደል አንኳር ምክንያቶቼ እነዚህ ነበሩ ።

የአንድ ውጥን ጥሩነት የሚለካው በንድፉ ማማር ሳይሆን በውጤቱ በመሆኑ፣ ካሰላስልኳቸው ግቦች አንፃር የጉባኤው ውጤት ምን ያህል ሰምሮልኛል? እንደ እውነቱ ከሆነ መቶ በመቶ ማለት ማጋነን አይመስለኝም ። ጉባኤው የአለም አቀፍ አመራር አባላት ተሸምግለው ወደአንድነት ጠረጴዛው እንዲመጡ ከመወሰኑም በላይ ፣አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ለትግሉ ያደረገውን አስተዋፅኦ አመስግኖ የድርጅት ጉዳይ ሃላፊነቱን ይዞ እንዲቀጥል ተስማምቷል ። በቅንጅቱ አለምአቀፍ ትግሎች ውስጥ በድጋፍ ድርጅቶች ውስጥ ያገለገሉ ወጣቶችና ሴቶች ወደምክርቤቱ የሚገቡበት መንገድ እንዲጠናና ምክርቤቱ በተማሩ ወጣቶች አቅም እንዲጠናከር ውሳኔ አስተላልፏል ። በሃገር ቤት በሰፈነው አፈና አስገዳጅነት በየጊዜው ሃገራቸውን ጥለው ለመሰደድ የሚገደዱ የቅንጅት አመራር አባላት ያለምንም ማመንታት የአለም አቀፉ ምክርቤት አባል ሆነው የሚያገለግሉበት ሁኔታ እንዲመቻችና፣ እነዶ/ር ሙሉአለምን የመሳሰሉ ምሁራን አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችሉበት መንገድ እንዲጠረግ ያቀረብኩት ሃሳብ በመርህ ደረጃ ተቀባይነት አግኝቶ፣ አፈፃፀም ላይ ግን ከሃገር ቤት ቅንጅት እያጣራን የሚል ውሳኔ ሊተላለፍ ችሎአል ። በ«ትብብር ለነፃነትና ዴሞክራሲ» የተጀመረው የተጓጎለ ሥራ እንዲቀጥል፣ በሊቀመንበሩ ሥር ልዩ ኮሚቴ ሃላፊነቱን ወስዶ በትኩረት እንዲሠራው ወስኗል ። በጉባኤው ያልተገኙት ወገኖች ደግሞ ተሳትፈውበት ቢሆን ኖሮ፣ ውጤቱ ይበልጥ ባማረ ነበር። በመቅረታቸው የተጎዳነው፣ የጉባኤው ተሳታፊዎችና ድርጅታችን ቅንጅት ነው ።

ይህ ከሳምንት በፊት በሽምግልና ተፈታ ተብሎ የተፈረመበት ቀለም ሳይደርቅ እንደገና ወደጥርጣሬና ፀብ የሚያመራው የቅንጅት ቁስል መንስኤ ምን ይሆን? በኔ አመለካከት ከቅንጅት ባህሪው የመነጨና፣ ይህ የሚጠይቀው እርጋታና አደብ የሌለ መሆኑ ነው ። ቅንጅት፣ ሊበራል ዴሞክራሲንና ሶሻል ዴሞክራሲን በሚያቀነቅኑ የቀስተደመናና ኢዴፓ ሃይሎችና በአማራ ህዝብ ድርጅት መሠረት ላይ በተገነባው የመኢአድ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኞች ጥምረት የተመሠረተ ፓርቲ ነው። በጤነኛ ሃገር፣ ምናልባት እነዚህ የፖለቲካ ሃይሎች እንኳንስ ወደ አንድ ፓርቲ ሊጠቃለሉ፣ አብረው ለመስራትም ላይጣጣሙ የሚችሉ ናቸው ። ሆኖም የኢትዮጵያ ልዩ ሁኔታ ባስገደደው ምክንያት፣ እነዚህ ሃይሎች አብረው ለመሥራት ወስነዋል ። ከተለያየው ፍልስፍናቸውም የሚመነጩ የድርጅታዊ አሠራር ልምዶችና እምነቶች አላቸው ። አንዱ ወገን የሊቀመንበሩን ሥልጣን አግዝፎ ሲያይ፣ ሌላው ከግራ ቅሪቱ ይዞ ከመጣው «የጋራ አሠራር» መርህ አኳያ ሊቀበለው ያዳግተዋል ። አንዱ በጓደኛ፣

ዘመድ፣ መሃላ፣ ባህልና ትውፊት ላይ ሲያተኩር፣ ሌላው ወገን በመርህ፣ በዴሞክራሲ፣ በግልፅነት ወዘተ ላይ ይንጠለጠላል ። ምናልባት የኢትዮጵያ ሃቅ ሁለቱም ጎራ ውስጥ ተሰንቅራ ይሆናል ብዬ እጠረጥራለሁ ። በዴሞክራሲ ተስፋዋና በኢትዮጵያ ብሄርተኝነቷ መሃል ። አንዱን ጥላ ሌላውንም አንጠልጥላ አይመስለኝም የወደፊት ጉዞዋ ። ስደተኛ እናት ነው የምትመስለኝ ። ብላቴናዋን በአንቀልባ፣ ማሙሽን በደረቷ ተሸክማ የምትማስን አይነት ። ልጆቿ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ብለው በደረቷና ጀርባዋ ላይ እንዲጣሉባት አትሻም ። እናት ናትና ማዳላትም አይሆንላትም ። ሁለቱን ማባባልና ማስታረቅ ብቻ ነው ምርጫዋ ። የቅንጅት ስቃይ ይህ ይመስለኛል ። በአንቀልባ የተሸከመውን የዴሞክራሲ ተስፋና፣ በደረቱ የያዘውን የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት አስማምቶና አዋድዶ መሄድ ነው ያቃተው ። ይህ በአንድ ገፁ የኢትዮጵያም አበሳ ጭምር ነው ። ምን ይሻላል?

መነጣጠሉ አንድና ቀላሉ መፍትሄ ሆኖ ሊሰማ ይችላል ። የስንፍና መንገድ ሁሌም ቀላል ነው ። የሰነፎችን መንገድ ግን ብንመርጥ «አለባብሰው ቢያርሱ ባረም ይመለሱ» እንደተባለው ነው የሚሆንብን ። የቀረበልንን ፈተና ተቀብለን በድል መወጣት ነው የጀግና ሥራ ። ዴሞክራሲ ናፋቂዎቹም ለብሄርተኞቹ ፍርሃትና ልማዳዊ የአሠራር ዝንባሌዎች ቦታ መስጠት፣ ብሄርተኞቹም ለቀድሞ ግራዎችና ለልዝብ ዴሞክራሲ ጠበቆች ስሱ መሆንና የሚገባቸውን ከበሬታም አለመንፈግ ነው መሃከለኛው ጎዳና ። በአናሳ አገዛዝ የምትናጠውም እናት ሃገር ይህን ዝቅተኛ መከባበር ትጠይቅ ይመስለኛል ። በአንዱ ወይም በሌላው ጎዳና ብቻ ተኪዶ የሚገኝ የፅድቅ ገዳም የሚገኝ አይመስለኝም ። የህይወት ቀለም ጥቁር ወይም ነጭ ሳይሆን ግራጫ ነው የሚባለውም ለዚህ ይመስለኛል ። ከሁለቱም ያጣቀሰ መሆኑን ለማስረገጥ ነው እንዲያ መባሉ ። በ«ኢ.ቲ.ኤን» ቴሌቪዥን ላይ አቶ ብርሀነ ወጥተው፣ «ቅንጅት አንድ ብቻ ነው»፣ ከኔ በቀር ሌላ አምላክ ያመነ ወዮለት ማለታቸው ትክክል አይደለም ። ቅንጅት 1001 ነው ። ቅንጅት የተጀመረ እንጂ ያላለቀ ውብ ስዕል ነው ። ቅንጅት ንድፍ ነው ። ብራናውን የወጠሩትን እያንጓጠጡ፣ ብሩሽ ያቀበሉ የሚወደሱበት ዘመን፣ ዘመነ ሃሴት ነው ። የቅንጅት ስቃይ አንድ ወጥ ፓርቲ ለመሆን በሚያደርገው ጉዞ፣ ገና ከመጀመሩ ብዙ ደንቃራዎች የገጠሙት፣ ከፓርላማ እስከ ናይንዝ ስትሪት «ያም ለኔ ያም ለኔ» ብለው የሚሻሙት፣ መሆኑ ነው ። ቅንጅት ሰቀላ ሳይሆን ዳስ ነው ። እንጨትና ሳር እየረበረቡ በቀላሉ የሚያሰፉት ። ለዚህ ዳስ የሚመጥንም ሆደሰፊነት የሚጠይቅ ይመስለኛል ። ያላለቀውን ሥዕል በጋራ እንጨርሰው ዘንዳ ።

ለምክርቤቱ ጉባኤ መካሄድ የቀረበው ትልቁ ተቃውሞ፣ «መሪዎቻችን ሊፈቱ ሳምንት ሲቀራቸው፣ ለአንድ ሳምንት ሥልጣን ምን አራወጣችሁ» የሚል ነው ። እርግጥ ነው የቀድሞው አለም አቀፍ አመራርም ሆነ የዛሬ ሳምንቱ የአለምአቀፍ አመራር ለዕላይ ምክርቤት የሥልጣን ምንጭ ቃሊቲ ነው ። ቃሊቲ ሲፈርስ ይፈርሳሉ ። ይህ ለጉባኤው ተሳታፊዎች በጣም ግልፅ የሆነ ጉዳይ ነበር ። ሆኖም ለብዙዎቻችን ሳምንት መጠበቅን ያላመንንበት፣ ወያኔ ቃሉን ያከብራል ብለን ለማመን የሚያስችል ምክንያት ስላልነበረን ነው ። ጉባኤው ላይ ሳይሳተፉ እንደቀሩት ወንድሞቻችን፣ ወያኔ በድርድር መሪዎቻችንን ይለቅልናል ብለን ለመጠበቅ ፈቃደኛ ባለመሆናችን ነው ። የመሪዎቻችንን ክብር ሳይነካና በህዝብ ፊት ሳያዋርዳቸው፣ ፓርቲውንም ይበልጥ ለመከፋፈልና ለማዳከም ያመቸኛል ብሎ ሳያሰላ፣ ወያኔ መሪዎቻችንን ይፈታል ብለን ማመን አልተቻለንም ። በድርድር ሳይሆን በምህረት፣ ወደቅድመ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ተስፋ ሳይሆን ወደ ድህረ ምርጫ ብካይ ባዘመመ መልኩ ነው ሊፈታቸው የሚችለው ብለን ስለጠረጠርን ነው ። ቢፈታቸው እንኳ፣ መብታቸው ተከብሮ፣ የፖለቲካ ሰብእናቸው ተጠብቆ፣ ቅንጅትን እንደገና ለማደራጀትና ለመመምራት የሚችሉበትን ሁኔታ ተቀብሎ ይፈታቸዋል ብለን ለማመን ምክንያት ስላላገኘን ነው ። በድርድር መሆኑ ቀርቶ፣ እድሜ ልክ ከፈረደባቸው በሁዋላ በምህረት የሚለቃቸውም ከሆነ፣ ወያኔ ላወጀው «የሸዋ ምሁራንን ትምክህተኝነት

መደምሰስ» ስትራተጂ በሚጠቅም መንገድ፣ «የነእገሌን የምህረት ልመና ተቀብዬ፣ የነእገሌን ግን አልተቀበልኩትም» ሊለን እንደሚችል፣ የወያኔ መሠሪነት የ32 አመታት ታሪክ የሚያስተምረን ብቸኛ ሃቅ በመሆኑ ነው ። ይህ እንግዲህ ውለን አድረን የምናየው ይሆናል ።

ሐተታዬን ስጀምር ጆሮዬ ላይ ስልክ ተጠርቅሞብኛል ብዬ ነበር ። የብርሃኑ አብሮ አደግ ነበር እንዲያ ያደረገው። «ስለ11ዱ ሰዎች ሹመት ብርሀኑ እንደማያውቅ ታውቃለህ ወይ?» ይለኛል ። «እንደዚያ ሊሆን እንደሚችል ጥርጣሬ አለኝ» ስለው «የለም ፋክቱን ነው የምነግረህ» አለኝ ። እኔም «ሰባ በመቶ እንደዚያ ሊሆን እንደሚችል እኔም ግምቱ ነበረኝ...» ስል ስልኩ ጆሮዬ ላይ ጥርቅም አለ ። መላልሼ ብደውልም አያነሳም ። እጅግ በጣም የማከብረው ሰው ስለሆነ ሃዘን ተሰማኝ ። አዎን! የ11ዱን ምሁራን መጨመር ያበሰረው ደብዳቤ ሌሎቹ የአመራር አባላት ያልመከሩበት ሊሆን እንደሚችል እያወቅሁ ነው ጉባኤው ላይ የተሳተፍኩት ። እንኳንስ ቅንጅቱ በሚገኝበት አጣብቂኝ ቀርቶ፣ አጣዳፊ ሁኔታዎችም በተፈጠሩበት ጊዜ መሪዎች ሳያማክሩ የሚሰሩባቸው ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ ። በቅንጅቱ ልዩ ሁኔታ ደግሞ፣ መሪዎቹ እስር በሚማቅቁበት በዚህ ወቅት፣ አቶ ሃይሉ በህክምና ሳቢያ ከሌሎቹ ተነጥለው በነበሩበት ሁኔታ፣ ለሽምግልና የላኩዋቸው ልኡካን፣ «እነዚህ ሁለት ቡድኖች መሃል የከረመው ፀብ አብሮ የማያሰራቸው ደረጃ የደረሰ በመሆኑ፣ ከሁለቱም ወገን ያልሆኑ፣ ከቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ውጪም የሆኑ ምሁራን ቢቀላቀሉበትና ሰፋ ያለ ምክርቤት ቢቋቋምና አዲስ አመራር ቢመርጥ ይሻላል፣ የነዚህንም አስራ አንድ ሰዎች ብቃትና ግብረገብነት አጥንተን አቅርበናል» ብለው በላኩላቸው መዘርዝር (ሪፖርት) መሠረት ነው፣ የሁለቱን የላዕላይ ምክርቤት አባላት ሃሳብ ተቀብለው ያፀደቁት ። ይህ አቶ ሃይሉን በወንጀለኝነት ያስጠይቃል ብዬ አላምንም ። ከአንድ መሪ የሚጠበቅ ውሳኔ ነው ያደረጉት የሚል እምነት አለኝ። ይህንን የሊቀመንበሩን ውሳኔ መፃረር የሚፈልጉትም የነ«አቶ ብርሀነ ቡድን» አባላት፣ ጉዳያቸውን ወደ ፓርቲው መሪዎች እንጂ፣ ወደ ድጋፍ ድርጅቶች ውሳኔና ወደአበዱ የዲሲ መገናኛ ብዙሃን ይዞ መንጦልጦል አልነበረም የሚጠበቅባቸው ። ይህ ሃላፊነት የጎደለው እርምጃ ነው የሚል ዕምነት አለኝ ። የፓርቲውን ሊቀመንበር ውሳኔ፣ በድጋፍ ድርቶች ማስወገዝ ከንቱ ቀቢፀ ተስፋ ይመስለኛል ። በስሜትና በንዴት የተነዳ እርምጃ ነውም እላለሁ ።

### ከእንግዲህ ወዴት?

አቶ ሃይሉ በድርጅቱ ሊቀመንበርነታቸው የመሰላቸውን እርምጃ ወስደዋል ። በዚህ ላይ ቅሬታ ያለው የፓርቲው አባል፣ ጉዳዩን የፓርቲ አባላት ወዳልሆኑ የድጋፍ ድርጅቶች ወስዶ ሊቀመንበሩን ማስወገዝ ሳይሆን፣ የሊቀመንበሩን ውሳኔ እየፈፀሙና እያስፈፀሙ ቅሬታቸውን ለፓርቲው አመራር ማቅረብ ነው ። እኔ የማውቀው የፓርቲ ዲሲፕሊን የሚጠይቀው ይህን ብቻ ይመስለኛል ። የማውቀው የፓርቲ አሠራር የግራ ስለሆነ፣ ሃሳቤ ግራ ግራ ይሸት ይሆናል ። በሃያ አመታት «የዴሞክራሲ» ስደቴም ግን የተለየ አልተማርኩም ። በስደት ሀገረ አሜሪካም ቢሆን የዴሞክራቲክ ፓርቲው የአመራር ችግሮች ደጋፊያቸው በሆነው የመምህራን ማህበር መድረክ ሲብጠለጠል አላየሁም ። ይህ የተሞከረው የዛሬ 28 አመታት በአውሮፓና አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ድርጅቶች ነው ። የኢህአፓ መሪ ተደርገው በየአህጉሩ ኮሚቴ የሚሠሩት ሰዎች ናቸው፣ የፓርቲውን ጉዳይ በተማሪ ማህበር መድረክ አስወግዘውና ሆ! አስብለው ትግሉን የበተኑት ። ያ በደስታ ፓርቲውን ያወገዘ ተማሪ ግን በትግሉ አልቀጠለም፣ እር በርሱ ተጫጨሆ፣ የቻይናና የአልባኒያ ተባ ድኖ ለመክሰም አመት አልፈጀበትም። ዛሬም በቅንጅቱ ድጋፍ ድርጅቶች ዙሪያ የተያዘው መጯጯህ፣ የተሻለ ዴሞክራቲክ ቅንጅትን ሳይሆን፣ በርስ በርስ ጩኸቱ ተደናቁሮ ተስፋ የሚቆርጥ ዜጋን ነው የሚያመርተው ። ሁኔታው ሃላፊነትን ይጠይቃል ።

የሊቀ መንበሩን ውሳኔ ለማክበር እንደ እሬት የሚመራቸው ወገኖች ያላቸው ሌላው አማራጭ ፓርቲውን ጥሎ መውጣት ነው ፡፡ ይህ ግን የሰነፎች ምርጫ ነው ፡፡ በተለይ ደግሞ በውጪ የፓርቲ ድርጅት ኖሮት የማያውቀው ቅንጅት፣ አቶ ብርሀነን የመሰሉ አደራጆች ጥለውት ቢሄዱ የሚያገኘው ጥቅም የለም ፡፡ ልምድና ችሎታቸውን ይፈልጋል ፡፡ ያዳበሩትን የአመራር ክህሎት ይሻል ፡፡ ሻለቃ ዮሴፍ ሊቀመንበርነቱን ለዶ/ር ታዬ እንደለቀቁት ሁሉ፣ አቶ ብርሀነም ፀሃፊነታቸውን ለአዲሱና ብቁው ምሁር ማስረከብ ይኖርባቸው ይሆናል፣ ይህ ግን ለቅንጅት ቤተሰብ አዲስ ተስፋን የሚፈነጥቅ እንጂ ማንንም የሚያስቆጭ መሆን የለበትም ፡፡ አቶ መስፍን መኮንንም የዲፕሎማሲውን ሥራ በተሻለ ይሠራው እንደሆን እንጂ፣ ያበላሸዋል ተብሎ አይጠረጠርም ፡፡ አቶ አንዳርጋቸውም የድርጅት ጉዳይ ሃላፊነቱን እንደያዘ ቆይቶ የተከላቸውን ችግኞች ለአዝመራ ቢያበቃ እንጂ፣ በዚህ ሁሉ መተረማመስ አዝኖ ጥሎን ወደጥናተ ገዳሙ ቢገባ የሚጎዳው ቅንጅት ብቻ ሳይሆን እናት ሃገር ኢትዮጵያም ጭምር ናት ፡፡ ዕውነተኛው መንገድ የዕርቅ መንገድ ብቻ ነው ፡፡ ብቸኛው መንገድ የፍቅር መንገድ ብቻ ነው ፡፡ የቅንጅት ፍቅርነትና መንፈስነትም ትርጉሙ ይሄው ነው ፡፡ አባል ያልሆኑን ለፓርቲ መሪነት እያጨ፣ ግራና ቀኙን እያዋደደ፣ ብሄርተኝነትንና ዴሞክራሲን እያጣቀሰ የመንጎድ ፡፡  የነገ ሰው ይበለን ፡፡

ከላይ ግልፅ እንዳደረግሁት፣ እዚህ ጉዳይ ውስጥ «ጥልቅ» ያልኩት ሁለቱን ሃይል ለማገናኘት ድልድይ እሆናለሁ ብዬ በማመን ነው ፡፡ እንደሚታወቀው ግን ጉባኤው ውስጥ ያልተገኙት ወገኖች፣ የንዴትና እልህ ኢላማቸው ያደረጉት እኔና ዶ/ር ታዬ ወልደሰማያትን ነው ፡፡ ላለምኩት የድልድይነት ሚና በምክርቤቱ ዘንድ ያገኘሁትን ተቀባይነት ያህል ከነ«አቶ ብርሀነ ቡድን» ካላገኘሁ፣ የስደት መቧካት ውስጥ ስሜንና ክብሬን ለማጉደፍ ፈቃደኛ አይደለሁም ፡፡ ማዕዴ ሙሉ ነው ፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሆኑ ወጣት ልጆች አባት ነኝ ፡፡ ትኩረቴን የሚፈልጉበት አደገኛ እድሜ ላይ መሆናቸው ይረዳኛል ፡፡ በሙያዬ ገና መፍካት የጀመርኩበት ደረጃ ላይ ነኝ ፡፡ ትኩረቴን ብሰጠው ልመነደግ የምችልበት ማማ ላይ ነኝ ፡፡ በ«መወያየት መልካም» የኢ.ቲ.ኤን ቴሌቪዥን ነፃ ግልጋሎቴ፣ የእንግዶቼን ስራ ለማጥናት በሳምንት ከ20 ሰአት  ያላነሰ ጊዜ አጠፋለሁ ፡፡ በጡረታ እድሜዬ የምሠራው ሳጣ ፖለቲካን የመረጥኩ ሰው አይደለሁም ፡፡ ሃገሬ ከአንድ ዜጋዋ ከምትጠብቀው በላይ፣ በአፍላ እድምዬ፣ በ23ና 33 አመት የጉብዝና ዘመኔ፣ ለአስር አመታት በበረሃ ተንገላትቼላታለሁ ፡፡ ድጋሚ ፖለቲካን የማነፈንፍበት ምክንያት የለኝም ፡፡ ቀስተ ደመና እንደተመሠረተ ከኢትዮጵያ ውጪ የመጀመሪያው አባል ነበርኩ ፡፡ በምርጫ ዘመቻውም ወቅት በሸዋና ወሎ በተደረጉ የቅስቀሳ ዘመቻዎች ከነዶ/ር ብርሃኑ ነጋና ሻለቃ አድማሱ ጋር ተሠማርቻለሁ ፡፡ በሬዲዮና ቴሌቪዥን ህዝብን ለመቀስቀስ የሚረዱ የፖለቲካ ማስታወቂያዎች ሥራ ላይ ፓርቲውን አግዣለሁ ፡፡ ዛሬም መጠነኛ አስተዋፅኦ ላድርግ ስል፣ ለሥልጣን የተዳረሰ ፓርቲ አጓጉቶኝ ሳይሆን፣ ራስ ራሱን በመቀጥቀጥ ላይ ያለ ፓርቲ አሳዝኖኝ እንጂ ነው ፡፡ ሁለቱ የአለም አቀፍ ሃይል ወደአንድ መድረክ መጥቶ የሚሠራበት ሁኔታ ሲመቻች፣ የኔ አስፈላጊነት እንደሚያከትም አምኜ በጊዜ ገደብ የገባሁበት ጉዳይ ነው ፡፡ ባለፉት ሃያ አመታት ስደቴ የተማርኩት ነገር ቢኖር፣ ከስደት ፖለቲካ ተሳትፎ የሚመረተው ውርደት መሆኑን ጠንቅቄ ስለማውቅ ልሸሸው ካልሆነ፣ የሚስበኝ ነገር አይደለም ፡፡ ከድርጅት ይልቅ በብዕሬ የተሻለ እንደማበረክት አውቃለሁና ፡፡ ለነፃነቴም እጅግ ቀናኢ በመሆኔ፣ ያን ሊያስተናግድ የሚችል ድርጅት ይኖራል ብዬ ስለማላስብ፣ የፓርቲ አባልነትም ሆነ አመራርነት የሚመጥነኝ ነገር አይደለም ፡፡ ምናልባት ጋዜጠኝነት የተሻለ መድረኩን ያመቻችልኛል፣ ጥሩ ጅኒም በውስጤ እንዳለ ይሰማኛል ፡፡ የኢትዮጵያን ማህበረሰብ በዚያ ዘርፍ የምሰጠው ነፃ ግልጋሎት ከበቂ በላይ ነው የሚል ዕምነት ስላለኝ፣ የስደት ፖለቲካ ውስጥ ለመናቆር ጊዜና አቅሙ የለኝም ፡፡ የመጨረሻ ቃሌም ይሄው ነው ፡፡